# በኮንዶሞች ጨዋታ ተዝናንተናል

ይነጋል በላቸው

*መግቢያ፡-*

ከፈረንሣይ ሉዊሶች አንደኛው ባደረበት የሴሰኝነት አባዜ የተነሣ ሴት በእጅጉ ያበዛ ነበር አሉ፡፡ በዚያም ምክንያት በሐውልት የሚመሰለው ማዕከላዊ የሰውነቱን ክፍል ከርክርና ጨብጥን ባለኮዳና ቂጥኝንም የመሳሰሉ የአባለዘር በሽታዎች ክፉኛ ይገዘግዙበት ጀመሩ አሉ፡፡ ተፈጥሯዊ ዐመሉ ላስከተለበት ለዚህ ክፉ የአመንዝረኝነት ልክፍት ቀዳሚ መፍትሔው ያን ክፉ ዐመል ማስወገድ ሲሆን ሲገባው ለሐውልቱ ሽፋን እንዲያፈላልግለትና ዋልጌነቱን እንዲቀጥል ሐኪሙን ጠርቶ አማከረው አሉ፡፡ በዚያን ፈታኝና አሳሳቢ ወቅት የግል ሐኪሙ ሐውልቱ ላይ የሚጠለቅ የዝናብ መከላከያ ከእንስሳት አንጀት አበጅቶ ሰጠውና ከጭንቀቱ ገላገለው አሉ፡፡ ያ ዶክተር ስሙ ኮንዶም ይባል ስለነበር ንጉሡን ከጭንቀቱ የታደገው የዚያ መከላከያ ስምም በዚያ ዶክተር ተሰየመና ‹ኮንዶም› ተባለ አሉ፡፡ ያልተጣራ ነገር ሲነገር በ‹አሉ› ከተጀመረ በ‹አሉ› ማለቅ ስላለበት ነው ‹አሉ›ን ያበዛሁባችሁና ይቅርታ፡፡

ይህን ታሪክ ብዙዎቻችን ሰምተናል፡፡ ከእማሬያዊ ትርጉሙ በወጣ ሁኔታ በዘመናችን የኮንዶምን ፍቺ ለጠጥ በማድረግ በሌሎች ዘርፎችም ለምሳሌ በፖለቲካው መስክ በስፋት እንጠቀምበት ይዘናል፡፡ ‹መጠቀሚያ›፣ እንደሸንኮራ አገዳ ተመጦ ሲያበቃ አገልግሎቱ ሲቀንስ ወይም መናጀነቱ ሲያበቃ ወይም የጥርጣሬና ያለመታመን ዐይን ውስጥ ሲገባ ወይም ወደተፈጥሮ ጤንነቱ ሲመለስ ተሸቀንጥሮ የሚጣል› ሰው በዚህ ስም ይጠራል፡፡

ዛሬ ዛሬ ዕድሜ ለአእምሮአዊ የንቃተ ኅሊና ደረጃችን ይህንን ስም በአደባባይ ለመጥራት ቀርቶ ገዝተን ለመጠቀምም አናፍርም፡ ፡ ዕድሜ ለኤች አይ ቪ/ኤድስና ለሚዲያዎች፡፡ ጥንት ግን እንኳንስ ገዝተን ልንጠቀምበት ስሙንም በ‹ቄስ ይጥራው› በእንትን ብቻ እንዘለው ነበር - ስንት የሚታፈርበት ነገር ሞልቶ በማይታፈርበት እያፈርን፡፡ … መግቢያየ አለቀ፡፡

## ሐተታ፡-

ዛሬ ዕለቱ 24.07.2004 ነው፡፡ ይህ ተዓምረኛ ቁጥር ደግሞ በትናንትናው ዕለት በተካሄደው የፌዝ የእግር ኳስ ጨዋታ የኮንዶም አርቲስቶች ቡድን ‹ሰይጣናዊ› ኮድ ነበር፡፡ ትናንት በአዲስ አበባ ስታዲየም በ‹ባለሥልጣናት›ና በ‹አርት› ሰዎች በተካሄደው ጨዋታ የቡድኑን አሰላለፍ በተመለከተ በዋና ‹አሰልጣኑ› በኮንዶም ሠራዊት ፍቅሬ ቀድሞ የተገለጸ የእግር ኳስ ጨዋታ አሰላለፍ ነበር ይህ ቁጥር፡፡ የባለሥልጣናቱን ሜዳው ላይ በኢቲቪ መስኮት ከተመለከትኩት ውጪ ቀድሞ ሲነገር አልሰማሁም፡፡ ስገምተው ግን 666 ሳይሆን እንደማይቀር እገምታለሁ፡፡ በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ ትልቁ ሰሞነኛ ሎተሪ እንደወጣና 666,666 ብር ለሁለት ይሁን ለሦስት ባለዕድሎች እንደተሰጠ በዚሁ ቲቪ ትናንትና ያን የቀልድ እግር ኳስ ስመለከት በተላለፈ የብሔራዊ ሎተሪ ማስታወቂያ ሰማሁ፡፡

በኮንዶሞች ጨዋታ ተዝናንተናል አልነበር መነሻዬ? አዎ፣ በበኩሌ እንደማሽላዋ እያረርኩ ነው የተዝናናሁት፡፡ በአቶ መለስም ቀናሁ - ከዚህ በላይ ምኞትን ማሳካት እኮ የለም፡፡ የዚህ የቀልድ ጨዋታ ሃሳብ ማንም ያመንጨው ነገር ግን አጽዳቂው መለስ ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ አለበለዚያ በውስኪና በቢራ የተጠበሰ ጉበትና በጮማ የተደፈነ ልብ ይዞ ለመጫወት አይደለም ለመመልከትስ የትኛው ደፋር ባለሥልጣን ነው ወደካምፖሎጅ የሚገባ? ደግነቱ ጠቅላላ ጨዋታው 36 ደቂቃዎች ብቻ መሆኑ፡፡ ቢፈርጡብንስ?

የጨዋታው ዓላማ ለዚሁ መከረኛ የአባይ ግድብ ገቢ ለማስገኘት ነው፡፡ እንደኔ ግን ይሄ ውጫዊው ቅባት ነው፡፡ ዋናው በምንም መንገድ ኢሕአዴግን ሊደግፍ የማይችለውን የአዲስ አበባን ሕዝብ በኮንዶሞቹ ጥረት ከዚሁ ሀገር ሻጭና በታኝ የሩቅ ብዕሲ መንግሥት ጋር ለማዋደድ የሚደረግ ግን የማይሣካ ጥረት ነው፡፡ በአማርኛ ብሂል ‹ እግሬን መትተው ራሴን ቢያኩኝ አይገባኝም› ይባላል፡፡ ከ21 ለሚበልጡ ዓመታት እንደእባብ እንደተረቱ እግሩን ብቻ ሣይሆን መላ አካሉን ሲቀጠቀጥ የኖረና አሁንም ባልተወለደ አንጀት በመሪር አገዛዝ እየተንገፈገፈ የሚኖር ሕዝብ ከእንግዲህ ወያኔ ማርና ወተት ቢያዘንብም እንኳን፣ ‹ከሕዝብ ጋር ሊታረቅ አይችልም› ብዬ ነው በበኩሌ ‹አቋም የወሰድኩት›፡፡ አቋም መውሰድ የወያኔ ቋንቋ ናት፡፡ ስንትና ስንት አቋም ወስደዋል መሰላችሁ፡፡

የጨዋታው ድባብ ምን ይመስል ነበር? ብዙ የራስ ቅሎችን ታዝቤያለሁ፡፡ በዳኝነቱ በኩል ሣተናው ኮንዶም ኃይሌ በጥሩ ሁኔታ መርቷል፡፡ ‹እሽ አትበሉኝ የሹም ዶሮ ነኝ› የሚሉ መስሎት ሳይሆን አይቀርም ለሹም ኮንዶሞች አድልቶ አንድ በግድ ያኮነዶሙትን አርቲስት በቀይ ካርድ ማስወጣቱን አልወደድኩለትም እንጂ፡፡ በነገራችን ላይ፤ የለም የለም አዲስ መስመር ልስጣት ይቺን ሃሳብ፡፡

በነገራችን ላይ ያኔ ጥንት በጣሊያን ወረራ፤

**ልጅ አሳድግ ብዬ ከብት እነዳ ብዬ፤**

**ሚስቴን ለሹም ዳርኩኝ እህቴ ናት ብዬ፡፡**

እንደተባለው - ከባለሥልጣናቱ ወገንም ይሁን ከአርቲስቶቹ ኮንዶም ለመሆን ፈልገው ሣይሆን እንዲጫወቱ ሲጠየቁ ምንተፍረታቸውንና የወያኔውን ቅያሜና ብቀላን በመፍራት ሳያምኑበት ወይም በገርነት ‹ሰውን ማዝናናት ምን ክፋት አለው› ከሚል የዋህነት በንጹሕ ኅሊና ተነሳስተው የገቡበት ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አምናለሁና አሁኑኑ ይቅርታቸውን እጠይቃለሁ - ምናልባት ይህችን ማስታወሻ ካነበቡ ወይ ከሰሙ ማለቴ ነው፡፡ ‹እስኪያልፍ ያለፋል› ነውና የተወረወረን ጦር ጎንበስ ብሎ ማሳለፉ መጥፎ አይደለም፡፡ እኔን ጨምሮ ብዙዎቻችን በዚህ መልክ ነውና እስትንፋሳችንን እያቆየናት የምንገኘው በደል ሳይፈጽሙ አንገትን ደፍቶ እንደምንም ዛሬን በነገ መተካት ጥፋት አይመስለኝም፡፡ የተቻለው ግን ከእንቅልፉና ከአዙሪቱ እየነቃ ለሀገር ነጻነት የድርሻውን ጥረት ቢያደርግ በታሪክና በትውልድ ይወደሳል፡፡ ልጆቹም ይባረካሉ፤ ከማፈር ይልቅ በወላጆቻቸው አኩሪ ድርጊት ይኮራሉ፡፡ ይህን ስል ግን ወደውና ፈቅደው በኮንዶምነት ለማገልገልም ተፈራርመው የሚያዘጠዝጡ አንፋሽ አከንፋሽ እንዳሉ ልደብቅ አለመፈለጌንም ማሳወቅ እወዳለሁ፡፡ በቂ ሀብት እያላቸው መጨመር ሲቻል በቂ ሀብት ብሎ ነገር ባለመኖሩ ለዚያ ሲሉ፣ በቂ ዝናና ታዋቂነት እያላቸው መጨመር ሲቻል በቂ ዝናና ታዋቂነት ብሎ ነገር ስለሌለ ለዚያም ሲሉ… ሰማይንና ምድርን ጠቅልለው ቢሰጧቸው አንዳችም እርካታ

የሌላቸው የአእምሮ ድውያን ዜጎች ወያኔ ጋር እየተጎናበሱ በሕዝብ ሥቃይ የሚነግዱ ወገኖች ግን ወዮላቸው! ከማለት በስተቀር ለጊዜው ልንለውና ልናደርገው የሚቻለን የለም፡፡ እነሱ ዛሬ ከውስኪ ውስኪ (ዋይት - ሬድ - ብሉ - ግሪን...) ከጮማ ጮማ ቢያማርጡ አብዛኛው ሕዝብ ግን በርሃብና በክፉ አገዛዝ ኤሎሄ እያለ እንደሆነ በውስጡ ሆነን የመከራና የሥቃዩ ተቋዳሽ የሆንነው ዜጎች ከካምፖሎጀው ፈንደቅያ በመለስ በሚገባ እናውቃለን፡፡ ይህ የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ እኔም አሁን ብዕሬን ያነሳሁት ጨዋታውን በጨዋታነቱ ነቅፌ ሣይሆን ይህኛው ማኅበረሰብዓዊ ጎን እንዲታወስ በመፈለጌ ነው፡፡ እንጂ የነአባዱላን ማራዶናዊ የኳስ ጥበብ የተላበሰ ፍጥርና አብዶ እንዲሁም የጎል አገባብ ማየትን ማን ይጠላል? - እናንተዬ ምናሜ (አባዱላ) እንዴት ተሸናቅጧል ጃል! ምን ነካውና ነው ግን እንዲህ ሙንን እያለ የሄደ? ለበጎ ያድርግለት፡፡

በአሰላለፉ ላይ ያለኝ ዕይታ፡- ከሐውልቶቹ ባለሥልጣናት ዋና ዋናዎቹ አልተካተቱም - በተለያየ ምክንያት ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ፡፡ አንድ ነገር ቢያንስ ሁለት መልክ አለውና እንደኔ እንዲህ ሊሆን የቻለው ለአንዳቾ ተንኮል መሆን አለበት፡፡ አብዛኞቹ ባለሥልጣናት ከምርጦቹ ዘር ያልሆኑበት ምክንያት - መሰለ የተባለው ኮንዶም የስፖርት ዘጋቢ የተወለዱበትን (ዕንቆቅልሽ ነው የሆነብኝ በውነቱ - ታዞም መሆን አለበት) አካባቢ እየገለጸ ሲዘግብ እንደተከታተልኩት አቶ መለስ ‹ይሄውላችሁ፣ ባለሥልጣኖቻችሁ የራሳችሁ የመሀል ሀገር ሰዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በላይ ሥልጣንን ማስረከብ ምን ይባላል?› ብሎ እንደለመደው ሊያላግጥ ይመስላል፡፡ ለነገሩ እንደኔ አስተሳሰብና እንደውነቱም ከሆነ የሰዎቹ ጥን አመጣጥ ከአድዋ ወይም ከእንጅባራ የመሆኑ ጉዳይ አይደለም፡፡ የችግሩ መባቀያ የሰዎቹ ማንነት ሳይሆን ሀገርን የማስተዳደር ብቃት ላይ ነው(ትምህርት፣ዕውቀት፣ችሎታ፣ልምድ...)፡፡ ወደጀመርኩት የመለስ የቁጭ በሉ ሥሌት ስመለስ ... ከዋናዎቹ ሐውልቶች ይልቅ ቅድሚያ በመስጠት እነዚህን ግልገል ኮንዶሞች ለጨዋታ ያሰለፋቸው የጠቀስኩትን የመሰለ ምክንያት ስላለው ነው እላለሁ፡፡ አለበለዚያማ እርሱ ራሱ ቤተ መንግሥት ውስጥ በጫት ወይም በሀሺሺ ምርቃና ውስጥ መሸጎ በቲቪ መስኮት ከሚከታተል ማጥቃት ልማዱ ነውና በደንብ የሚያውቃትን 11 ቁጥር ማሊያ ለብሶ አይጫወትም ነበር? ማን ከለከለው? ያ እነማንን ነበር እናንተዬ ‹አርቀን ቀብረናቸዋል› እያለ ባላስፈላጊ ሁኔታ በየአክሲዮን ስብሰባው የሚዘላብደው ሣሞራ የሎስ እሚባለው ሰውዬ ከኋላ ማሳደዱን በደንብ ስለሚያውቅበት 4 ቁጥር ለብሶ በተርሲንነት አይሰለፍም ነበር? ሥዩምስ? በረከትስ? ቴዎድሮስ አድኃኖምስ? ስብሃት ነጋስ? አዲስ ዓለምስ? የተጋቡት ወያኔዋ የተከበሩ ኮንዶም ገነት ዘውዴስ? ... ቱባ ቱባውን ሐውልትና ተፈራንና አዲሱን የመሰሉ ኦሪጂናል ኮንዶሞችን አስቀምጦ በታዛዥ አዳዲስ ኮንዶሞች ሜዳ መግባትን ምን አመጣው? ንቀት ነው? ‹የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ›ና ‹ምክትል ጠ/ሚኒስትሩ›ስ ብቻቸውን በዚያ የተከበረ ካምቦሎጆ ተገኝተው የኮንዶም አርቲስቶችን ጨዋታና የሕዳሴ ዘፈን መመረቅ ነበረባቸው? ግፍ አይደለም? የ‹ሀ› ቡድን ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆኖ እየሣቀብን በ‹መ› ቡድን እንድንዝናና የተደረገው ለነሱ ‹መ›ም ሲበዛባቸው ነው ተብሎ አይደለም? ወይንስ እነሱ እሚገጥሙት ሌላ ያላወቅነው ቡድን ይኖር ይሆን? ሞት ይርሳኝና አባባ ግርማስ በውነት በጤና ካሉ በአጥቂነትም ይሁን በተከላካይነት መሰለፍ ባይቻላቸው እንኳን በቡራኬ ሰጭነት በክቡር ትሪቢዩኑ ቢገኙ እንደፅድቅ ይቆጠርልን አልነበረም? እውነት ግን የሳቸው ነገር እንደ እስራኤሉ ፕሬዝደንት እንደኤሪየል ሻሮል ሆነሳ! ለምን ያስጨንቁናል? ለምን ቁርጡ ተነግሮን ሀዘናችንን በቅጡ አንወጣም ወይም ፈጣሪ የአመራር ዕጦት ችግራችንን ተመልክቶ ዕድሜያቸውን ስለቀጠለልን በደስታ አንቦርቅም? ‹በተሟላ ጤንነት ላይ ናቸው› እያሉ ዜጎችን እንቁልልጭ ማለት መነሻው ምን ይሆን? የምንስ መደባበቅ ነው? ከሆስፒታል አልጋም ይሁን ከሞርቼዋሪ ይውጡና የሚሆነው ይሁን - ያበጠው ይፈንዳና ይለይልን፤ ማቅ መልበስ በኛ ተጀመረ? መሪን አልቅሶ በገዛ መሬቱ መቀበር አዲስ ነገር መሆኑ ነው? መቼም ጠቢቡ ሶሎሞን እንደጨረሰው ከሰማይ በታች ከምድር በላይ አዲስ ነገር የለም፤ የተወራው እውነትም ቢሆን አፈር አያሟሹም፡፡ ምትክ እንደሆነ ሞልቷል - ዕድሜ ለዶን የጥርስ ህክምና ማዕከል፡፡ በዚያ ቦታ ጥርሱን የነቀለ አንዱን ያመጣልናል - ማዕከሉ፡፡ ... (የማይቋጭ) የደምና የድራማ ምድር - ኢትዮጵያ!

ሕዝቡን በተለይም ወጣቱን ግን ምን ነካው? ዘፋኞቹ ጥዑመ ዜማቸውን ሲያንቆረቁሩለት እንደተደገመበት ሰይጣን ፀጥ ማለቱ ለደግ ነው? ብዙ የተለፋበትንና ቀን ከሌት የተደከመበትን ዝግጅት ማቀዝቀዝ ምን ይባላል? ወይንስ በእግረ መንገድ እንደወትሮው ሁሉ አንዳች መልእክት እያስተላለፈ ይሆን? ጠርጥሬያለሁ፡፡ ዘፋኞቹ ላንቃቸው እስኪበጠስ ይጮሃሉ ሰው ግን የተነጋገረ ይመስል ፀጥ አለ፡፡ ምናልባት የኔ የሚላቸውን አርቲስቶች አጥቶ ቢሆንስ - እንደነቴዲ አፍሮ ያሉ የሕዝብ ፈርጦችን - ? እንደዚያ ከሆነ ለነዚህ በባዶ ሜዳ እንደቁራ ይጮሁ ለነበሩ አርቲስቶች ትልቅ ትምህርት ነው፡፡ ዳሩ ሲማሩ አይደል? አሁን ቢማር ቢማር ሠራዊት ይማራል? ያ የልጅ ልጅ ልጆቹ የሚሆኑ ሕጻናት ሴቶች ልጆችን ይዞ ቅንጣት ሣያፍር በየዳንስ ቤቱ - ዕድሜውን ይቀጥሉለት ይመስል - በስተርጅና ዓለሙን እሚቀጨው ቅሌታሙ ባለካባ ሰውዬስ ከአሁን በኋላ ዓለም ታልፋለች እንጂ ሊማር ይችላል? እንዴት ብሎና በየትኛውስ ሂሳብ? ብዙ ድፍን ቅል እኮ ነው ያለው በሀገራችን፡፡ ከላይ የበከተ ሥርዓት - ከሥር መሠረቱ የበሸቀጠ ማኅበረኢኮኖሚያዊ መዋቅር ዱሮውንስ አበቅቴው ካልተሻረ መች ጤንነት ሊገኝና - እየበሰበሰ ያበሰብሳል እንጂ፡፡ ግን አይዞን፡፡ የቀኝ ኋላ ዙሩ የቆዬ ደንብ አይጣስምና በትግስት - በማተቡ - የጠና የታጋሽነቱን ምንዳ አያጣም፤ በዚህም ይሁን በዚያኛው፡፡ እኒህኛዎቹም ‹ቀበጥ አማት ሲሆ ብትር አላት› ነውና አሁን በተገፋው ሕዝብ ላይ ቢያሽቃንጡ እንዲህ እንደሆንን የምንቀር አይደለንምና የሚከፍሉት ዕዳ አለባቸው፡፡ ማን በማን አላግጦ ይቀራል? አሁን ሁሉም ነገር በነሱ ቁጥጥር ስለሆነ እንዳሻቸው ይፈንጩ፤ ይቦርቁም፡፡

ብዙዎቹ ተጫዋቾች ባለሥልጣናቱም ላይ ሆነ አርቲስቶቹ ላይ ውስጣዊ ብርሃን አላነበብኩም፡፡ የውስጥ ፀዳላቸው አልወጣም፡፡ ያ ምን ያሳያል? የሕዝቡ እውነተኛ ችግርና የሚሠሩት ቲያትር አልጣጣም እያላቸው ውስጣቸው እየተጨነቀ ይሆን? አልዋሽም ይህንንም ጠርጥሬያለሁ፡፡

በመሠረቱ ግድብ መሥራት ብርቅ አይደለም፡፡ አንድ ግድብ ይህን ያህል አገር ይያዝልኝ እሚያስብል ሆኖ ሳይሆን እነአቶ መለስን እንዲህ እያወራጨ ያለው - ሌላ ሊሸፍኑት የሚሞክሩት ጉዳይ ስላላቸው ነው፡፡ ይህን እውነታ ማንም ያውቃል፡፡ የኤሌክትሪክ ግድብ እነበርማና ኔፓልም አላቸው፡፡ ደቡብ አፍሪካ ብትሄዱ በየአምስትና አሥር ኪሎ ሜትሩ ትላልቅ ግድብ አታጡም ይባላል፡፡ እነሱ ግን ሕዝብን አልዘረፉም፤ ለየግድቦቻቸውም ጽላት ለማስቀረጽ እስኪደርሱ ድረስ በውዳሴና በሙገሣ የራሳቸውንም ሆነ የዜጎቻቸውን ልብ በከንቱ አላደረቁም፤ እንደወያኔ እጅ እጅ እስኪሉ አልፈነደቁም፡፡ ሥራን ትሠራዋለህ - ሠርተህም ታሳየዋለህ እንጂ እንዲህ በፕሮፓጋንዳ ሰውን ቋቅ እስኪለውና እስኪገለማው እያንገሸገሸክ እንደወያኔ ሙጥኝ አትልም፡፡ የወያኔዎች ሁኔታ ግን ‹እነዚህ ሰዎች ለይቶላቸው አበዱ እንዴ?› ያስብላል፡፡ አንድ ግድብ ይህን ያህል ሥራ አስፈትቶ በወሬ ቱልቱላ ይጠምዳል? ለሞኝ ሰዎች ይሄኔ እኮ ግድቡ ሲያልቅ ድህነትና ርሀብ ከሀገራችን ጓዙን ጠቅልሎ እሚወጣ ነው እሚመስላቸው፡፡ ውሸት ነው እባካችሁ፡፡ በኤሌክትሪክ መቆራረጥ እንዳሁኑ አንቸገር ይሆናል እንጂ በሌላው ወያኔ እስካለ ድረስ ያው ነው፤ እንዲያውም ይብሳል፡፡ ርሀብና ችግር የወያኔ

EthioLion.Com

የባሕርይ ስጦታዎች ነውና፡፡ ወያኔ ባለበት ችግር አለ፤ ወያኔ ባለበት ርሀብና መድልዖ አለ፤ ወያኔ ባለበት መለያየትና መከፋፈል አለ፡፡ በቃ፡፡ ሌላ የላቸውም፡፡ እንጂ ይህን የኛውን የአባይ ግድብማ ቢፈልጉ አቶ መለስ ራሱና ጥቂት ባለሥልጣናት(ከዘረፉትና በየባንኩ ካከማቹት) እንዲሁም ገንዘባቸውን የት እንጣለው እሚሉ ጥቂት ነጋዴዎች ቢያዋጡ በቀላሉ ያሠሩት አልነበረምን - የኛን የሽረሪት ድር የወረሰውን ባዶ ኪስ በግድ ከሚቧጥጡ? ቀልደኞች ናቸው፡፡ ቻርሊ ቻፕሊን የበለጡ የክፍለ ዘመኑ ቀልደኞች - ግን የቸኩና የጠነዙ ሞዛዛ ቀልደኞች ናቸው፡፡ የማናውቅ እየመሰላቸው ይሆናል፡፡ ያለው የሌለው ምን እንደሚለው እንዴት እንዳገኘው ምን እንደሚባልም አያውቅምና፡፡...

ቲያትሩ ላልተወሰነ ጊዜ ይቀጥላል፡፡ ኮንዶሞቹም አገልግሎታቸውን ላልተወሰነ ጊዜ ይቀጥላሉ፡፡ እኛም እንመዘግባለን - ለታሪክ እናስቀምጣለን፡፡ ‹ውሾቹ ይጮሃሉ፤ ግመሎቹም ጉዟቸውን ይቀጥላሉ›፡፡ የመለያ ምቱ ፊሽካ ሊነፋ የቀረው ጊዜ ግን እጅግ ቀርቧል፡፡ እንዲህ እንደመጥምቁ ዮሐንስ በምድረ በዳ የምንጮህ ወገኖች የሚታየን እየታየን ስለሆነ አትፍረዱብን፡፡ ጆሮ ያለው ይስማ፡፡...

---

ይህን ደብዳቤ እየላኩሁ ሳለ በኢትዮሜዳ ስለአማራ ተፈናቃዮችና ስለመኢአድ አቤቱታ አነበብኩ፡፡ ልቤም በሀዘን ታመመ፡፡ አማራ ስለሆኑ ወይ ስላልሆኑ አይደለም፡፡ በማንም የሰው ዘር ላይ የሚደርስ ግፍና በደል ያማል፡፡ በተለይ ደግሞ ዘረኝነትን በመርህ ደረጃ አንግቦ ለሌሎች ዘውጎች ዕልቂት ሆን ብሎ የሚሠራና ወንጀለኞችን እያሠለጠነ የሚያሠማራ ወንጀለኛ መንግሥት ሲገጥም ህመሙ ከሰውነት አይወጣም፡፡ችግረኞቹን እግዜር ያጽና፡፡ ሁሉ ነገር ለበጎ ነውና እነሱ ሞቱም ዳኑም በነሱና በሌሎችም ላይ የተፈጸመውና እየተፈጸመ ያለው ግፍ ጽርሐ አርያም ደርሶ የመጨረሻውን መፍትሔ ያሰጠን፡፡ ይህን ዜና ያቀረቡትን ሪፖርተርንና እሱን ጠቅሰው ያወጡትን ድረ ገፆች ፈጣሪ ይባርካቸው፡፡ ቀደሞውን አያድርስ ነበር እንጂ እሚባል አሁን ከደረሰ በኋላ ምን እንላለን? ወይ ግፍ!!!!

EthioLion.Com